# ፪. ከአንጾኪያ የትርጓሜ ትምህርት ቤት የወጡ መናፍቃን

ሀ ሉቅያኖስ

- የአንጾኪያ ትርጓሜ ትምህርት ቤትን የመሰረተ እና በትምህርት ቤቱም ለረጅም ዓመታት በማስተማር ያገለገለ ሰው ነው
- በትምህርቱም የግኖስቲኮችን የፍልስፍና ትምህርት አራማጅ ነበር

## የሉቅያኖስ ትምህርት፡-

- ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮት እንደሆነ በሥልጣንም የተካከለ መሆኑን አይቀበልም
- በተጨማሪም " ***ወልድ በጸጋ በማደጎ ከአምላክነት ደረጃ ደረሰ ፤ 'ከስጋዌ በፊት ቃል አካል ሳይኖረው በአብ አካል ውስጥ ይኖር የነበረ ዝርው ኃይል ነው። ..... የማርያም ልጅ ኢየሱስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ በአብ አካል ውስጥ የነበረው ዝርው ቃል መጥቶ አደረበት። ራሱ ባደረገው ተጋድሎ እና በሠራው ትሩፋት በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ ለመባል በቃ። እስከ መስቀል ድረስ አብሮት ከቆየ በኋላ ኢየሱስ ሲሰቀል ዝርው ቃል ተለይቶት ሔደ።'*** " ብሎ የሚያስተምረውን የጳውሎስ ሰማስጢን ሐሳብ የሚደግፍ ትምህርቱን መልክ ሰጥቶ ያቀረበው እርሱ ነው

# ከአንጾኪያ የወጡ•••••

- በዚህም መክንያት የእስክንድርያው ትምህርት ቤት ሙሁር እለእስክንድሮስ ሉቅያኖስ የጳውሎስ ሰማስጢ አልጋ ወራሽ ነው ሲለው
- የቤተክርስቲያን አባቶች እና ታሪክ ጸሐፊዎችም ሉቅያኖስን " ከአርዮስ በፊት የነበረ አርዮስ በማለት ይገልጹታል
- በ311 ዓ•ም ሞቷል

# ከአንጾኪያ የወጡ•••••

**ለ አርዮስ**

- በ3ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በ257 ዓ•ም በሊቢያ ተወለደ
- በቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ክርስቲያን የሆነበት ጊዜ ባይመዘገብም ክርስቲያን ነበረ
- ከ ቤተክርስቲያን የተለየበትን ትምህርት ያገኘው በአንጾኪያ ትምህርት ቤት ከሉቅያኖስ ነው
- ከ እስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ከነበረው ከተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ የዲቁናን ማዕረግ ተቀብሏል
- ቅዱስ ጴጥሮስ የዲቁናን ማዕረጉን ለ አርዮስ ከሰጠው በኋላ በአርዮስ ልቦና የተደበቀው ተንኮልና በእርሱ ምክንያት ቤተክርስቲያን እንደምትቸገር ተገለጠለት
- ይህ ቅዱስ አባት በራዕይ ቀሚሱ ለሁለት የተከፈለ ሕጻን መስሎ ጌታን ያየዋል " ልብስህን ማን ቀደደብህ" ቢለው " አርዮስ ልብሴን ቀደደብኝ" ብሎታል ይህን ማለቱ አርዮስ ከባህርይ አባቴ ከአብ ለየኝ ፍጡር ነው በማለት የባህርይ ገንዘቤን ገፈፈኝ ማለቱ ነው

# ከአንጾኪያ የወጡ•••••

- ይህን ራዕዩን ለተማሪዎቹ ለ አኪላስ እና ለእለእስክንድሮስ ነግሮአቸው አርዮስን አውግዞታል እነርሱም ምንም አይነት ግንኙነት ከአርዮሳውያን ጋር እንዳይኖራቸው ነግሯቸዋል
- ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ከተገደለ በኋላ አኪላስ መንበሩን ወረሰ በዚህ ጊዜ አርዮስ አኪላስን ተለማመጠው አኪላስም የጴጥሮስን አደራ ሳያከብር አርዮስን ተቀብሎ ቅስና ሾመው
- አኪላስ በመንበሩ ብዙም ሳይቆይ በአንድ አመቱ ሞተ የአኪላስ አሟሟት የመምህሩን የተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስን ቃልኪዳንን ባለመጠበቁ የመቅሰፍት ሞት ነው ይባላል

**የአርዮስ ትምህርት፡-**

- እግዚአብሔር ፈጣሪነት እንጂ ወላዲነት የለውም ቀዳሚ ጥንት የሌለው አብ ብቻ ነው ከእሱ በቀር ሁሉም የተፈጠረ ነው ይላል
- አብ አባት ተብሎ የተጠራው ከዘመናት በኋላ እንጂ ከዘመናት በፊት አብ አይባልም ነበር

# ከአንጾኪያ የወጡ•••••

፤ወልድ፤ ቃል በባህርዩ ፍጡር ስለሆነ ያልነበረበት ጊዜ ነበር

ብሔር ዓለምን ለመፍጠር ስላሰበ መፍጠሪያ መለኪያ እንዲሆነው አስቀድሞ ብብን ፈጠረ አንጥረኛ መዶሻውን ሸክላ ሠሪ መደቧን አስቀድማ ትሰራ ከፍጥረት ዓለም ጥቂት ቀደም ብሎ ወልድ ተፈጥሯል ይላል

ሁ ለመሆን የመጣው የመታዘዝ ግብር ስላለበት ነው

ወልድ የመጀመሪያ ፍጥረቱ እንደሆነ ለወልድም መንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ቱ ነው ይላል

ምንፍቅናው ከፍልስፍናው ሃሳቡ ውጭ ያስረዳልኛል ብሎ ያነሳው የመጽሐፍ ሳብ በምሳ 8፥22 ላይ " እግዚአብሔር ለሥራው የመንገዱ መጀመያ ፈጠረኝ " " ጥበብ ከፍጠረረቱ ሁሉ አስቀድሞ እኔን ፈጠረኝ አለች " ሁን ገፀ ንባብ ነው በዚህ ጥቅስ ላይ በአርዮስ ኣታረዳጎም ጥበብ የተባለው ነው ፈጠረኝ ያለውም እግዚአብሔር አብ ፈጠረኝ ማለት ነው ብሏል።

# ከአንጾኪያ የወጡ•••••

- ወልድ ለአብ ፍጡሩም ልጁም ነው  በመዋዕለ ሥጋዌ ባሳየው ታዛዥነት እና የተጋድሎ ጽናት ከእግዚአብሔር ቡራኬን ፣ጸጋን ተቀብሎ እንደጻድቃን ሰማዕታት ሱታፌ አምላክነትን አገኘ ይላል ።ስለዚህ ፍጡር ሲሆን በገድል በትሩፋት አምላክ ለመሆን አምላክ ለመባል የበቃውን እሱን እኛም አምላክ ነው ብለን ልንጠራው አምላክ ነው ብለን ልናመልከው እንችላለን  ብሏል
- በአርዮስ  አመለካከት መውለድና መፍጠር ሞክሼ ቃላት ናቸው እንጂ የተለያየ ትርጉም የላቸውም።
-

# አለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት

በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀዳሚና ተቀባይነት ያላቸው የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንም የምትቀበላቸው ጉባኤያት ሥስት ናቸው

1. ጉባኤ ኒቅያ በ 325 ዓ•ም
2. ጉባኤ ቁስጥንጥንያ በ 381 ዓ•ም
3. ጉባኤ ኤፌሶን በ 431ዓ•ም

# ጉባኤ ኒቅያ

- የኒቅያ ጉባኤ የተደረገው በ325 ዓ•ም ነው
- አርዮስ በዚህ ጊዜ እድሜው የገፋ ቢሆንም እንኳን ከአንጾኪያ ያመጣውን የክህደት ትምህርት ለማስተዋወቅ እንደ ወጣት ጎረምሳ ይራራጥ ነበር
- የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የአርዮስን የግል አስተሳሰብ ሳትቃወም ብዙ ቆይታለች እርሱ ግን ለህዝቡ በሚገቡ ቃላት በመጠቀም ሃይማኖት አዘል የሆኑ የግጥም ጹሑፎችን እያዘጋጀ ለእንጨት ሰባሪዎችና ለውሃ ቀጂዎች ለነጋዴውና ላራሹ ሁሉ ያድል ጀመር
- ሰውም ከስድ ንባብ ይልቅ ግጥም ማንበብ ስለሚወድና በግጥም ያነበበውም ስለማይጠፋው በዚህ እየተሳበ የአርዮስን ክህደት ሳያውቀው ገባበት
- አርዮስ የክህደት ትምህርቱን የሚያስተላልፍበት የግጥም መጽሐፉ "ታሊያ " ይባላል ማዕድ ማለት ነው
- አርዮስ በዚህ መጽሐፉ ልብወለድ ፍልስፍና እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ለራሱ አስተሳሰብ እንዲስማማ አድርጎ የተረጎማቸውን ሃሳቦች ያሰፍርበት ነበር ምሳ 8 ፡23

# •••••••ኒቅያ

- አኪላስ ከሞተ በኋላ  በመንበሩ የተሾመው እለእስክንድሮስ አርዮስን ከስህተት ትምህርቱ እንዲመለስ ብዙ ጥረትን ቢያደርግም አርዮስ ሊመለስ ባለመፍቀዱ አንድ መቶ/100/ ከሚጠጉ የሊቢያንና የእስክንድርያን ኤጲስ ቆጶሳት ሰብስቦ የክህደት ትምህርቱን ማስተማር በጀመረበት በ ሁለት ዓመቱ በ320 ዓ•ም አውግዘው ለዩት
- ይሁን እንጂ አርዮስ  እለእስክንድሮስ የሰባልዮስን ትምህርት ያሰተምራል እኔንም አውግዞ አባረረኝ እያለ ነገሩን  ለሁሉ አዳረሰው
- የኒቆሜዲያ ኤጲስ ቆጶስ የነበረው  እና ከአርዮስ ጋር ከሉቅያኖስ  የተማረው ጓደኛው አውሳብዮስ   አርዮስን ወደ ኒቆሜዲያ ጠርቶ በአከባቢው ያሉትን ኤጲስ ቆጶሳት ሰብስቦ  እራሱ በመራው ጉባኤ አርዮስ ከእስክንድርያ የተባረረው በግፍ ነው ብለው ከውግዘቱ ፈተነዋል አሉ
- አርዮስም ወደ እስክንድርያ ተመልሶ  እለእስክንድሮስ ቢያወግዘኝ ተፈትቼ መጣሁ በማለት የክህደት ትምህርቱን ማስተማር ቀጠለ
- ይህ አለመግባባት ሥር በመስደዱ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ  የእስፓኝ ጳጳስ ሆስያስን ወደ እስክንድርያ ልኮ ነገሩን ካጣራ በኋላ  ጠቡ የሃይማኖት እንጂ የስልጣን አለመሆኑን አውቆ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ እንዲደረግ  አዋጅ አስነገረ።

# •••••••ኒቅያ

- በአዋጁ መሰረት ብዙ ኤጲስ ቆጶሳትና ሊቃውንት  በኒቂያ ተሰባሰቡ ከምዕራብ ከመጡት አምስት/5/ ኤጲስ ቆጶሳት ውጭ ሌሎቹ ከምስራቅ የመጡ ናቸው  ከእነዚህም መካከል ከእስክንድርያ እለእስክንድሮስና አትናቲዮስ የአንጾኪያው አዎስጣቴዎስ እንዲሁም የነጺቡን ያዕቆብ ይገኙበታል
- በጉባኤው ላይ የተገኙት  ቁጥራቸው በተለያዩ የታሪክ ጸሐፊዎች የተለያየ ቁጥር ቢገልጹም " ወልድ ዋህድ " በማለት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው የተገኙት 318 ብቻ ነበሩና ቤተክርስቲያን ይህን ቁጥር ትቀበላቸዋለች

# •••••••ኒቅያ

- ጉባኤው የሃይማኖት ውሳኔ የሚሰጥበት ስለነበረ እንደ ሐዋርያት ጉባኤ የኤጲስ ቆጶሳት ብቻ አልነበረም ።ሶዞሜን የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ እንዳቀረበው የግሪክ ፈላስፎችና፣አርጌንሳውያን የአርዮስ ደጋፊዎችም እንዳያሙ በብዛት፣ተጠርተው መጥተው ነበር ኦርቶዶክሳውያን ታዛቢዎች ግን ጥቂቶች ነበሩ ።
- ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት እንዲመሩ የተመረጡ ሶስት ሰዎች ናቸው
- የእስክንድርያው እለእስክንድሮስ፣ የአንጾኪያው ኤዎስጣቴዎስ እና አስቀድሞ የንጉስ መልዕክተኛ ሁኖ ወደ እስክንድርያ፣ሄዶ የነበረው የስፔን ኤጲስ ቆጶስ አስዮስ / ሆስዮስ ነው
- አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች የጉባኤው ሊቀመንበር ራሱ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ነበር ይላሉ ነገር ይህንን ሃሳብ የሚደግፉትበፊት ተረፈ አርዮሳውያን ዛሬ ደግሞ ጆሆባወያን ናቸው ይህን የሚሉትም አርዮስ የተረታው በንጉሱ ተጽእኖ ነው ለማለት፣ነው ስለ ክርስትና ዶግማ ምንም የሚያውቀው እና ያልተጠመቀው ንጉስ የጉባኤው ሊቀ መንበር ነበር ማለት አያስኬድም (ወደፊት አንደምናየውም) ንጉሱ ቆስጠንጢኖስ ከአትናቴዎስ ጋር በነበረው አለመግባባት ይታወቃል ።
-

# •••••••ኒቅያ

- **ጉባኤው መጀመሪያ የተጋገረበት አንቀጾች**

1. አርዮስ የቀረባቸውን ጥቅሶች መመርመር
2. አርዮስ ጥበብ የሚለውን ቃል እንዴት እንደተረጎመው ማየት
3. ወልድ በባህርይው ፍጡር ከሆነ በማዳን ምሥጢር ላይ ስለሚያደርሰው አደጋ።
4. እግዚአብሔር ቃል ለሰው ልጆች ሲል ወዶ ያደረገውን ተዋርዶ አርዮስ የባሕርይ ተወራጅነት ቢኖርበት ነው ስለማለቱ
5. ወልድ በባሕርዩ ፍጡር ሳለ እንደሌሎቹ ፍጡራን በገድል በትሩፋት የአምላክነትን ክብር አገኘ ስለማለቱ

# ••••••• ኒቅያ

- **አርዮስ ባነሳቸው ሃሳብ ላይ የጉባኤው ምላሽ**
- አርዮስ እና ግብሩ አበሮቹ የግሪኮችን ፍልስፍናና ከመጽሐፍ ቅዱስም ለእነሱ እንዲመች አድርገው የተረጎሟቸውን ምሳሌ 8÷24 ና የመሳሰሉትን እየጠቀሱ ስለ ወልድ ፍጡርነት ሞክረዋል
- እነ አትናቲዮስ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒት ነው አዳኝ ነው ማዳኑን ካመንክ የባህርይ አምላክነቱን ማመን አለብህ የሚያድን እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስመስክራል እያሉ ያስተባብሉበት ነበር
- በማቴዎስ ወንጌል ያለውን ቃል በማንሳት "በማቴዎስ ወንጌል የተማርነው የጠፋው በግ ምሳሌ መላውን የሰው ዘር የሚመለከት ነው ፈላጊውም ቃል የእግዚአብሔር ልጅ ነው ቃል ፍጡር ከተባለ የጠፋው እርሱም ራሱ ነው ፍጡር ደግሞ ራሱ መዳን ስለሚያስፈልገው ፍጡርን ማዳን አይችልም
- በእርሱ መዳናችንን ካመንን ግን ያደነን እርሱ አምላክ እንደሆነ ማወቅ እና ማመን አለብን ብለዋል
-

# •••••••ኒቅያ

- አርዮስ በጉባኤው ላይ " በገድል በትሩፋት ስለ ከበረ አምላክ ተብሎ ሊሰገድለት ይገባዋል ብሎ ለተናገረው ሲመልሱ
- ክርስቶስ ከባህርይ አባቱ ከአብ ጋር አንድ ነው ይህ ካልሆነ ግን ማለትም ፍጡር ነው ካልን ለሱ የአምልኮት ስግደት ማቅረብ አምልኮ ባዕድ ነው ሲሉ ሃሱቡን ተቃውመዋል
- በተጨማሪም ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም፣እንኳን ወልደ እግዚአብሔር ወልደ አዳም ብንለውም እርሱም በመዋዕለ ሥጋዌ ሐዋርያትን ወንድሞቼ እያለ ቢጠራቸውም የአብ የባህርይ ልጅነቱን ሲናገር " አባቴ" "አባታችሁ" አለ እንጂ "አባታችን " አላለም አብም ልጁን በደብረ ታቦር እንዲሁም በዮርዳኖስ አብረውት፣ከነበሩት ጋር "ልጆቼ" ብሎ አልተናገረም "ልጄ" ብሎ ጠራው እንጂ በማለት ተናግረዋል
- ከዚህ በኋላ ጉባኤው የአርዮስ ሃሳብ ሰው ሰራሽ በምርምር እና በፍልስፍና የተቃኘ እንጂ ከእግዚአብሔር አምላካዊ ምስጢር ጋር የማይዛመድ በመሆኑ ለቤተክርስቲያን በተሰጣት ሥልጣን እና መብት አውግዘው ለይተውታል።
- በስተመጨረሻ በጉባኤው የተገኙ ሊቃውንት አንቀጸ ሃይማኖትንጨደንግገዋል

# ••••••ኒቅያ

**የኒቅያ አንቀጸ ሃይማኖት**

1. በአንድ አምላክ እናምናለን ፣ሁሉን የያዘ አባት ሁሉን የፈጠረ የሚታየውን እና የማይታየውን
2. በእግዚአብሔር ልጅ በአንድ በኢየሱስ ክርስቶስም  እናምናለን ብቻውን ከአብ የተወለደ ይኸውም ከአባቱ ባህርይ ከብርሃን  የተገኘ  ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተወለደ እውነተኛ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ በመለኮቱ ከአብ ጋር አንድ የሚሆን  ሁሉ በእርሱ የሆነ
3. ስለ ሰዎች ስለ መዳናችንም የወረደ  ሥጋ የሂነ ሰውም የሆነ
4. ታመመ፣ሞተ ተቀበረ
5. በሦስተኛው ቀን ዳግመኛ ተነሳ
6. ወደሰማያት ወጣ
7. ሕያዋንና ሙታንን ይገዛ ዘንድ ዳግመኛ የሚመጣ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን